# <u>አማራ የኢትዮጵያ አስኳል</u>

በነሲቡ ስብሐት (703 300 4302) USA, VA መጋቢት 19 ቀን 2015 ዓ.ም. (March 28, 2023)

መጋቢት 16 እና 17 ቀን 2015 ዓ.ም. (March 25,26, 2023) በሰሜን አሜሪካ ስፐሪንግ ፊልድ፣ ቨርጂንያ በተካሄደው *"ታላቁ የአማራ ጉባኤ በሰሜን አሜሪካ (Grand Amhara Convention in North America)"* በአካል ተካፈልሁ። ይህንን ጉባኤ በጥሞና በመከታተል ምን አገኘሁ? ላልነበሩትና ላሉትም እይታዬን ማጋራት ወደድሁ። በተለይ በሀገር ቤት በአለው የኦነግ/ወያኔ ጥምር አገዛዝ አበሳውን እያየ ላለው የኢትዮጵያ ሕዝብ እና በተናጠል እየታረደ እየተጨፈጨፈ ላለው አማራ ሕዝብ ስሜቴን በማጋራት የጉባኤውን ሂደት ምልከታዬን ትንሽ ልበል።
የዚህ ጽሁፌን ርዕስ ያደረኩት የሁለት ቀኑን *"የታላቁ አማራ ጉባኤ"* በአንድ ቃል ላስቀምጠው ፈልጌ ነው። አዎ! አማራው ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ ያደረጋት ሕዝብ በመሆኑ ነው *<u>"አማራ የኢትዮጵያ አስኳል"</u>* ያልኩት። ኢትዮጵያን ጠላት እያደረጉ ትግል ያካሄዱት ህወሓት እና ኦነግ እንቁላሉን በመስበር ኢትዮጵያችንን ለማፈራረስ አስኳሉን ለማፍሰስ/ለማምከን አማራን በየተራ ከገደል ሲወረውሩት፣ ሲያርዱት፣ በጅምላ ሲፈጁት፣ መካን ሲያደርጉት የኖሩት፤ አሁንም እያደረጉ ያሉት። ነፍሳቸውን ይማርና ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ጉዳዩ ተገልጾላቸው ወያኔ እና ኦነግ በሽግግር መንግሥት ስም ሥልጣን መያዝ እንደጀመሩ ማግስት ነበር አማራው ተደራጅቶ እራሱን ይከላከል ዘንድ የጠቆሙትና ፈር የቀደዱት።

አማራ ብሎ በመደራጀት ኢትዮጵያን የምናጣት እየመሰለን ትኩረት ባለመስጠታችን እነሆ እስከዛሬ ያላባራው የአማራ እልቂት ኢትዮጵያን ሊያፈራርሳት እያኮበኮበ ነውና ኢትዮጵያን የምናድናት ለፍትህ የተነሳው አማራ *"እኛው ነን!"* ብሎ መንቀሳቀሱ ጥሩ ጅምር ነው እላለሁ።

"እንዴት ከኢትዮጵያዊነት ወደ ዘር?" ለምትሉ ቀና ብለን እንመልከትና ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ ያሰኛት አማራ መሆኑን ለመናገር መድፈር ይኖርብናል። አማራ ከትግሬ የኖረ፣ ከኦሮሞ የተጋባ፣ ከጉራጌ የጨፈረ፣ ከአፋር የተቃቀፈ፣ ከደቡብ አብሮ የኖረ፣ ለጋምቤላው፣ ለሱማሌው፣ ለሀደሬው መብት የጮኸ ወዘተ. እንጂ እንዴሌሎች ጠባቦች አስተሳሰቡን ያጠበበ አልነበረም፤ አይደለምም። ሊቀጠቀጥና ሊጠፋም የተፈረደበት ይኸው ኢትዮጵያዊነት ስሜቱ በአድዋው ጦርነት፣ በማይጨው ጦርነት በከፈለው መራር መስዋዕትነትና በጥቅሉ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር በማስቀጠሉ ከፍተኛው ዋልታና ምሰሶ በመሆኑ ነው። ሆኖም "ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ!" እያለ ህወሓት/ኦነግ ዘረኛ ቡድን ሲያጠቃውና የእኩይ ተግባራቸው ዒላማ ሲያደርጉት በአማራነቱ ተንቀሳቅሶ ሀገሩን ማስመለስ ይኖርበታል። *<u>አማራ ሀገሩም ሆነ ዘሩ ኢትዮጵያ ነች</u>*።

መለስ ብለን የወያኔ/ህወሓት የ27 ዓመት አገዛዝ ውስጥ በየጊዜው እየተፈጠሩ የከሰሙ ወይም ስም እየቀያየሩ የሚንከባለሉ ድርጅቶችን በተለይ በውጭው ዓለም በገንዘቡ፣ በእውቀቱ፣ በጉልበቱ በተጨማሪ የሚደረጉ ስብሰባዎችን በማድመቅ ከፍተኛው ድርሻ የአማራው ነበር። "ኦነግ ተቀይሬሃለሁ" ሲል፣ "ወያኔዎች ከመለስ ተጣላን" ሲሉ ሀገሩን ይፈልጋልና አብላጫውን ድጋፍ የሰጣቸው አማራው እንደነበር የሚዘነጋ አልነበረም። ሁሉም ግን እየተጠቀሙበት ሊያጠፉት ከማሴርና ከመምከር አልፈው እያስጨፈጨፉት ይገኛሉና አማራነቱን ከፍ አድርጎ ሀገሩን ማዳን እንደሚገባው ይህ ጉባኤ ያሰመረበት ጉዳይ ነው።

ኢትዮጵያን ለመበታተንና እንደሀገር እንዳትቀጥል ሦስቱ የጥቃት ዒላማዎች አማራ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነትና፣ የምኒልክን ታሪክ ማጠልሸት ናቸው።አማራው ከሁሉም ኅብረተሰብ ጋር ተባብሮና ተከባብሮ ሀገሩን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የማስመለስ ሃላፊነትና ግዴታ አለበት። በመሆኑም ሰሞኑን የተካሄደው *"የታላቁ አማራ ጉባኤ"* እሰየው የሚያሰኘው ከዚህ ምልከታው አንፃር ነው። ዘርን ተመርኩዘው የሚያጠቁትን ወያኔ/ኦነግ መሰል ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ከመመከት አልፎ ሀገርና ሕዝብ ሊያድን የሚቻለው *"እኔው ነኝ!"* ብሎ እየመረራቸው አማራነቱን ሲያሳያቸው ነውና ይበል ብያለሁ።

*ውድ ወገኖች፡- በዚህ **“ታላቁ የአማራ ጉባኤ”** ላይ በወጣው የአቋም መግለጫ ቁጥር 4 “መወሰድ ስለሚገባቸው አስቸኳይ እርምጃዎች ጥሪ” በሚለው ርዕስ የሰፈረው “በኢትዮጵያ ላይ የተጫነውን አኖጋዊ አፓርታይድ አገዛዝ ማስወገድ አማራጭ የሌለው የወቅቱ ጥያቄ ነው። ለዚህም የአገዛዙ ጥፋት አጀንዳ ዋና ዒላማ የሆነው የአማራው ሕዝብ ተደራጅቶና በአንድ ላይ ሆኖ በታመነ ስልት እየተመራ ትግሉን ማካሄድ አለበት። የአማራው ሕዝብ መሠረታዊ ግብ ከተሰነዘረበት የተቀናጀና ሁለገብ ጥቃት እራሱን መከላከልና ከበባውን ሰብሮ ክብሩን መብቱንና ጥቅሙን ማስጠበቅ ብሎም ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ወገኖቹ ጋራ ተባብሮ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን ማድረግ ነው።እነዚህን ዓላማዎቹን እውን ለማድረግ ማንኛውንም ሰብአዊ፣ ተፈጥሮአዊና ሕጋዊ እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ነው።በዚህም መሠረት በአጭር ጊዜ ውስጥ አማራው ሌሎችም ለፍትህ የቆሙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የሚከተሉትን አስቸኳይ እርምጃዎች እንዲወስድ ጥሪ አቅርቧል።”* ይላል፤ የጥቅሱ መጨረሻ ሥርዝ የተጨመረበት።

ከላይ በተጠቀሰው ጥሪ መሠረት ኢትዮጵያ እንደሀገር እንድትቀጥል ካስፈለገ አማራው የመንግሥት ስልጣንን በእጁ አስገብቶ ከፊታችን የተደቀነውን አስከፊ የውድመት ድግስ ለማምከን መረባረብ የሚጠይቀን ወቅት ላይ ነን። በ***“ታላቁ የአማራ ጉባኤ”*** ላይ ሀሳብ እንደሰጠሁት ሁሉ የጉባኤው ዋና ዓላማ ***“ዓለም አቀፍ የአማራ ንቅናቄ”*** (Amhara Movement) በመመሥረት ያለውን ጥምር የወያኔ/ኦነግ/ብልጽግና አገዛዝ ማውደም ነው። የታቀደው ***“የአማራ ንቅናቄ”*** ስኬታማ ይሆን ዘንድ ደግሞ የታዩኝን ሦስት ነጥቦች ላስቀምጥ፡-

1. **ጠላት ማነው?** የሚለውን በመመለስ ማታገያ መፈክር ማስቀመጥ የመጀመሪያው ሀሳቤ ነው። ወያኔ/ህወሓት አሁን ደግሞ ብልጽግና/ኦነግ “አማራ ጠላታችን” ብለው በፈጠሩት ንቅናቄ ሥልጣን ይዘው ለ32 ዓመት ሀገርና ሕዝብ ከማተራመስ አልፈው የመጨረሻው የውድመት ደረጃ ላይ ሀገራችንን አድርሰዋል። ይህንን የጥፋት መንገድ በመቀልበስ ***“የአማራው ንቅናቄ”*** ውጤታማ እንዲሆን ካስፈለገ የንቅናቄው ዋና ጠላት የህወሓት/ወያኔ/ብልጽግና/ኦነግ ዘረኛ ቡድን መሆኑን ተገንዝቦ በዘር የተዋቀረው **“የህወሓት ሕገ መንግሥት ይውደም!”** *መሪ መፈክር መሆን ይገባዋል* እላለሁ።በዚህ ግብ ሀገራችን ከዘረኝነት ወደ ኢትዮጵያዊነት የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ***“የአማራው ንቅናቄ”*** ቀዳሚ ሚና መጫወቱ አግባብነት ይኖረዋል።

2. **ትብብር** ***“የአማራው ንቅናቄ”*** ትኩረቱን ሙሉ በሙሉ ሀገር ቤት አድርጎ ከጉባኤው አቅራቢ በቀረበው ገለጻ *መሠረት “አማራ ፋኖን በማጠናከር ይህ የወንበዴዎች አገዛዝ ሊገረሰስ የሚችለው በጦርነት ነውና ለዚህ ሙሉ ድጋፍ መሰጠት ይኖርበታል”* አባባል እያጠነከርኩ በተጨማሪ ከሃይማኖት ተቋማት ማለትም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር በአንድ በኩል፤ ከኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጋር በሌላ በኩል፤ የጠበቀ ትሥሥር በመፍጠርና የዚህን የዲያብሎስ አገዛዝ ወንበዴ ቡድንን እድሜ ለማሳጠር መረባረብ ያስፈልጋል።

3. ***ትግል መሪ ይፈልጋል።*** ትግል መስዋዕትነት ይጠይቃል። ***“የአማራ ንቅናቄ”*** ግቡ አድርጎ የተነሳውን ዓላማ ከጫፍ ለማድረስ ቆራጥ መሪ ማውጣት ይኖርበታል እላለሁ። በዚህ ***“የአማራ ንቅናቄ”*** የተሰባሰበው ኃይልና መላው የኅብረተሰብ ክፍል በሂደት ለሚዘጋጀው ወይም በግብታዊነት ለሚፈነዳው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አመራር በመስጠት የ32 ዓመቱ አገዛዝ ያበቃለት ዘንድ ንቅናቄውን ወክሎ ከፊት የሚጋፈጡ ታዋቂ ግለሰቦችን ማፍራት እንደሚገባ ልጠቁም እወዳለሁ። በቅርቡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋእዶ አባቶች ዘንድ የተጠራው ***“የጥቁር ቀን”*** ተግባራዊ ሆኖ አገዛዙን ያርበተበተው ሕዝባችን ምን ያህል ለእምነቱ ግንባሩን እንደማያጥፍ ያስመሰከረው በቅዱስ አባቶቹ ጽናትና መሪነት ነው። ይህ ቆራጥነትና የዓላማ ጽናት ለ***“አማራው ንቅናቄ”*** ትግል ሊውል ይገባዋል። ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የግልና የመንግሥት ሠራተኞች፣ ምሁራን፣ ታክሲና ባጃጅ ሹፌሮች፣ ነጋዴዎች፣ እናቶች፣ አባቶች፣ ታዳጊ ሕጻናት፣ ***“የአማራ ንቅናቄው”***ን ድጋፍ እንዲሰጡና እንዲቀላቀሉ ብሎም ለሕዝባዊ ፍልሚያው ዝግጁ ይሆኑ ዘንድ ተሰሚና ግምባር ቀደም መሪ ያስፈልጋል።
***“የአማራ ንቅናቄ”*** ዓላማ፣ ራዕይ እና ተልዕኮ ያካተተ ማንፌስቶ በጉባኤው ለተገኙትም ሆነ ላልተገኙት ዋናው ማታገያና የንቅናቄው ዋልታ ነውና በአፋጣኝ ለእንቅስቃሴው አካላትና ለሕዝብ ይፋ መደረግ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

***"ታላቁ የአማራ ጉባኤ በሰሜን አሜሪካ"*** ለመከታተል በአካል የተገኘው በሺዎች የሚገመት አማራ ምን ያህል አማራው ለሀገሩ ያለውን ፍላጎትና ወቅታዊነቱን ያንጸባርቃል። በ1997 ዓ.ም. ምርጫ ዋዜማ በነበረው የቅንጅት እንቅስቃሴ ወቅት የነበረው ሕዝባዊ መነሳሳት ነጸብራቅ ነው ብል አልተሳሳትኩም።
***"የአማራ ንቅናቄ"*** በቀጣይነት ውጤት ተኮርና ስኬታማ ንቅናቄ በመሆን ለድል ይበቃ ዘንድ መታየት የሚገባው ጥንቃቄ ያልኳቸውን ላስቀምጥ፡-

1. ወያኔ/ኢሕአዴግ በተለይ ከ1997 ዓ.ም. የምርጫ ውጤት በኋላ በደም አንሰራርቶ ቀጣይ ሂደቱ የዲያስፖራውን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠርና ለመከፋፈል በሚልዮን የሚቆጠር ዶላር በመመደብ እና አስፈጻሚ አካላት ከሀገር ቤት ጭምር በማስገባት እንዴት እንደተጫወተ ትምህርት ልንቀምስበት የሚገባ የቅርብ ጊዜ ትዝታ በመሆኑ ይህንን ሂደት የብልጽግና/ኦነግ ቁንጮ መሪ በአለ በሌለ ኃይሉ ተጠቅሞ በዲያስፖራው ***"የአማራው ንቅናቄ"*** ይኮላሽ ዘንድ እንቅልፍ እንደማይተኛ በመገንዘብ ጠንካራ እና ታማኝ አመራር መፍጠርን ይጠይቃል።
2. ከዚህ ***"ዓለም አቀፍ የአማራ ንቅናቄ"*** በፊት በአማራ ስም የተመሠረቱና ሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ካሉ በዚህ ንቅናቄ ውስጥ ቢካተቱ የድሉን ጊዜ ያሳጥረዋልና ይታሰብበት እላለሁ። አሁን ሀገርና ሕዝብ ማዳን ነውና ቀዳሚው ለሥልጣን ስንል ኃይላችንን አንበታትነው። ሆኖም <u>ከዚህ ***"የአማራ ንቅናቄ"*** በኋላ የሚፈጠር ማንኛውም አማራ ነክ ድርጅት ተቀባይነት እንዳይኖረው በውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ ያሉ የንቅናቄው አካላት አጠንክረው መታገል ይኖርባቸዋል።</u> የተጀመረውን ማጠናከር ሲገባ ተደራቢ ለመፍጠር የሚጥሩ ወይ እንደ ወያኔ/ኢሕአዴግ ዘመን ብልጽግና/ኦነግ የገዛቸው አማሮች ከመሆን አይዘሉምና አባላቱና ደጋፊዎቹ ይህን ***"የአማራ ንቅናቄ"*** በሚገባ በማጠናከር በአጭር ጊዜ ለውጤት ለመብቃት የሚታይ ንቅናቄ መሆን ይኖርበታል።
3. በሰሜን አሜሪካ እና በካናዳ እንዲሁም በሌላው ዓለም ለሚመሰረቱ ***"የአማራ ንቅናቄ"*** ድጋፍ ኮሚቴዎች ከአመሠራረቱ ጀምሮ ዋናው አመራር አካል ቀጥተኛ ተሳትፎ ማድረግ ይኖርበታል።
4. ***"የአማራ ንቅናቄ"*** ተግባራዊ ለማድረግ በተካሄደው ጉባኤ የመጣውን ኃይል በአጭር ጊዜ ዓለም አቀፍ ታዋቂነቱን አጠንክሮ መሠረቱ ሀገር ቤት ለሆነው ፍልሚያ በመዘጋጀት በሚካሄደው ጉዞ ከዚህ በፊት በተለያየ እንቅስቃሴ ይታወቁ የነበሩና በሂደት የብልጽግናን ብልሹነት ተረድተው ጀሌ በመሆን ትግሉን የከዱ ቀደምት "ታዋቂዎች" ወደዚህ ስብስብ የተካተቱ እለት ንቅናቄው አቅጣጫውን እንደሚስትና እንደሚያበቃለት በእርግጠኝነት ልጠቁም እወዳለሁ።
5. ከአለፈው መማር ጥሩ ነውና "ከመለስ ተጣላን" ብለው በዲያስፖራው እንቅስቃሴ ውስጥ መሪ ያጣን ይመስል "ምሩን" ተብለው ሲጨፈርና ሲጨበጨብላቸው የነበሩ የወያኔ አመራሮች ዛሬ የት እንዳሉ ግንዛቤ በመውሰድ አሁንም ብልጠት ከከሸፈበት ዐቢይ አሕመድ "ተጣላን" ብለው ወደ ውጭ በመውጣት ተመሳሳይ የማዘናጋትና የመበተን ሚና የሚጫወቱ በቅርቡ ወደ ዲያስፖራው ሊላኩ ይችላሉና በጉባኤው እንዳየነው ንቅናቄው የታጋይም ሆነ የመሪ ችግር የለበትምና በሩን ከርችሞ ሥራው ላይ ማተኮር እንደሚገባ ማስገንዘቡ አይከፋም።
6. በመጨረሻም ለ***"አማራው ንቅናቄ"*** ስኬታማነት ገንዘብ ሊያጠያይቅ አይገባም። ***"አማራ ፋኖ"***ን በትጥቅና በሎጂስቲክ ለማጠናከር፣ ለቅስቀሳ ሚድያ (ማገር) እና ለሌሎች በርካታ ጉዳዮች ያስፈልጋልና መዘርዘር አያስፈልግም። ሆኖም አሁን ከአለው የኑሮ ውድነት አንጻር በተጨማሪ ዲያስፖራው ገንዘቡን ከስክሶ የከዱት በርካታ ናቸውና ***"የአማራ ንቅናቄ"*** አመራር የገንዘብ አያያዝና ተጠያቂነት ላይ ከጅምሩ ትኩረት ቢሰጡት ይጠቅማል።

*ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይጠብቃት!*
*የአማራው ንቅናቄ የሀገርና ሕዝብ ህልውና ጉዳይ ነው!*
*መጋቢት 19 ቀን 2015 ዓ.ም.* **(March 28, 2023)**
<u>*ኢሜል*</u>: nhsibhat@gmail